ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጫማ ሲለብሱ፣ ሲያበጥሩ፣ ሲፅዳዱና በሁሉም ጉዳያቸው ቀኝን መጠቀም ይወዱ ነበር።

ከአማኞች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች፦ «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጫማ ሲለብሱ፣ ሲያበጥሩ፣ ሲፅዳዱና በሁሉም ጉዳያቸው ቀኝን መጠቀም ይወዱ ነበር።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለማክበር የተገቡ የሆኑ ጉዳያቸውን ሲፈፅሙ በቀኝ መጀመርን ይወዱና ያስበልጡ ነበር። ከነዚህ ጉዳዮችም መካከል: ጫማ ሲያደርጉ በቀኝ እግር ይጀምራሉ፤ የጭንቅላታቸውን ፀጉርና ፂማቸውን ሲያበጥሩ፣ ሲቀቡና ሲያስውቡ በቀኝ ይጀምሩ ነበር፣ እጃቸውና እግራቸውን ዉዱእ ሲያደርጉም ቀኛቸውን ከግራ ያስቀድሙ ነበር።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3018